# ተራርቆ በመፊክር የትግል ትብብር ማድረጉ ወዴት ይወስደን ይሆን?

ትቅምት 9-2009 ዓ.ም.(21-10-2016)

ወያኔ በፈጠረው ቀውስ የተማረረው ሕዝብ በየቦታውና በየጊዜው እምቢ ብሎ ከተነሳ ወራቶች አልፈውታል።የተነሳሳው ሕዝብ የጋራ ችግር ቢኖርበትም፣አንድ አይነት ፍላጎትና ጠላት ቢኖረውም አሰላለፉና አካሄዱ ያው እንደሚታገለው፣ ለችግርና ለልዩነት በጎሳ ሸንሽኖ እንዳጋለጠው ጎሰኛ መንግሥት  እንደነደፈው ሆኖ ይታያል።እንቅስቃሴው ጎልቶ የታየው ኦሮሞ እና አማራ ክልል ብሎ ወያኔ በከፋፈለው  አካባቢ ሲሆን በሌሎቹም ቦታዎች ማለትም በጋምቤላ፣በኮንሶ፣በደቡብ፣በሓረር፣በድሬዳዋ...በከተማና ገጠር ሳይቀር ብሎም በራሱ በወያኔ ዋሻ በሆነው በትግራይ አንዳንድ ወረዳዎች ጭምር ተቃውሞው እየጠነከረ በመሄድ ላይ ነው።

ይህንን ተቃውሞ ለመግታት በሎም ለማጥፋት በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን ያልገለበጠው ድንጋይ የለም።ከማታለል እስከ መግደል ድረስ ከዚያም አልፎ አሁን በቅርቡ በሕዝቡ ላይ የክተት አዋጅ በጊዜያዊ ስም አውጆ ለመጨረስ ቆርጦ ተነስቷል።የሕዝቡ ትግል አንድ ጊዜ እየሞቀ ሌላ ጊዜ ቀዝቀዝ እያለ ከመሄዱ በስተቀር መንግሥት እንደተመኘው ሊሆንለት አልቻለም።አሁን ሰሞኑን ደግሞ ለለውጥ ተነስቻለሁ ብሎ እራሱን ከደሙ ንጹህ ለማድረግ የተለመደ ሰበካውን በሚያምናቸው መካከል ታጅቦ በድፍረት አደባባይ ወጥቷል።የሕዝቡን ኑሮ የማይኖሩትን ሰብስቦ ስለሕዝቡ ጥያቄና ችግር መፍትሔ ያመጣሉ ብሎ መነሳት ቀልድ ከመሆኑም በላይ ማን አለብኝነት ነው።በሕዝቡ ጥያቄና ትግል ላይ ውሃ ለማፍሰስ ፣በወያኔ ዘመነመንግሥት በተከፈተላቸው ዕድልና የሙስና ቀዳዳ ሃብታም የሆኑና ለመሆንም የሚሯሯጡ ግለሰቦችን ሰብስቦ መላ ምቱ ከማለት ይልቅ የጉዳዩን ባለቤት የችግሩን ገፈታ መጣጭ የሆነውን ሕዝቡን በጥይትና በዱላ ሳይሆን ለጥያቄው መልስ ለመስጠት መሞከር የሚሻል ነበር።የሕዝቡን አፍ አፍኖ የራሱ አውደልዳዮች የሆኑትን ስለሕዝብ ብሶት እንዲናገሩ ማድረግ በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት ያህል ነው።ያማል።

ሂደቱ እንደሚጠረጠረው ከሆነ የዘፈን ዳርዳሩ እስክስታ ነው እንደሚባለው በቅርቡ እነዚያኑ በዙሪያው ያሰለፋቸውን አስመሳዮች የሥልጣኑ ተካፋይ ለማድረግ የሚያስችል ካርታውን ይመዝ ይሆናል።ይህ ከሆነ ደግሞ ምንም እንኳን የሕዝቡን መሰረታዊ ጥያቄ ማለትም ሥር ነቀል ለውጥ ባያመጣም በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ዓለም የሚያዘናጋና የሚያምታታ ሁኔታ ሊፈጥር እንደሚችል አይካድም።

በዚህ ሂደት ደሙን እያፈሰሰ ሲታገል የቆየው ሕዝብ ምን ሊተርፈው ይችላል?ምንም የማይተርፈው ከሆነስ የጀመረውን ትግሉን እንዴት ይቀጥልበታል?እስከአሁንስ ባካሄደው ትግል ምን ተጠቀመ?ደካማና ጠንካራ ጎኑስ ምንድን ነው?

ህወሃት/ኢሕአዴግ በተለያየ ስልትና መልክ ቢመጣ ከቦታው እስካልተወገደ ድረስ ጉዳት እንጂ የሚሰጠው ጥቅም የለም፤የሕዝቡንም ጥያቄ አይመልስም።የሕዝቡ ጥያቄ የዲሞክራሲ ስርዓት ይመስረት፣የሕግ የበላይነት ይስፈን፤የሕዝብ እኩልነት ይረጋገጥ፣የዜጎች መብት ይከበር፣ማንኛውም ዜጋ በፈለገበት ያገሩ መሬት የመኖር፣የመሥራት፣ንብረት የማፍራት መብቱ ይረጋገጥ፣የአገር ዳር ድንበር ይከበር...የሚሉ ናቸው።እነዚህን ጥያቄዎች ደግሞ ለሃያአምስት ዓመታት ሥልጣኑን በጉልበት ይዞ የኖረው ህወሃት መራሹ ኢሕአዴግ ሊመልስ አይችልም፤ለመመለስም ተፈጥሮው አይፈቅድለትም።እነዚህን ጥያቄዎች ሊመልስ የሚችለው በሕዝቡ የተመረጠ፣የአገሩና የሕዝቡ ጉዳይ የሚያሳስበው፣የዴሞክራሲን ጽንሰሃሳብ ተረድቶ በተግባር የሚተረጉም፣አገር ወዳድና ሕዝብ አክባሪ የሆነ ፣በጎጥና በጎሳ ብሎም በክልል እይታ ያልታወረና ያልተለከፈ መንግሥት የሥልጣኑ ባለቤት ሲሆን ብቻ ነው።

ታዲያ ለዚያ አይነቱ መንግሥትና ስርዓት መስፈን የተበታተነው የሕዝብ ትግል ይረዳል ወይ? ቀምሮ በሳጥን ውስጥ ያስቀመጠውን ተንኮል የሚያከሽፍ ነወይ? በየቦታውስ የሚካሄደው የሕዝቡ ትግል ያንን የሚያበሰርና የሚያረጋግጥ ነውን? ብለን ብንጠይቅ በእኔ በኩል መልሱ አይደለም ነው። እርግጥ ነው በሥልጣን ላይ ያለውን ቡድን ሊያስጨንቀውና ሊያተራምሰው፣ትርምሱም ከበዛ ሊገረስሰው ይችል ይሆናል።ግን ሲገረሰስ አብሮት የሚገረሰስ አለወይ ብለን መጠየቁ ብልህነት ነው።ይህ ተንኮለኛ አገር አፍራሽ ቡድን ቢገረሰስ አገርና ሕዝብ በታትኖ ለመሄድ ደንታ የለውም።ደንታ ቢኖረውማ ኖሮ በሥልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የሚቃወመውን ሕዝብ ባልገደለ፣ባላሳደደ፣ባላሰረ ነበር።አሁንም ሕዝቡ ከዳር እስከዳር ተነስቶ የሚያቀርበውን ጥያቄ አዳምጦ መልስ በሰጠ ነበር።

በአሁኑ የሕዝቡ ትግል አካሄድ ይህ ቀበኛ ቡድን ቢገረስስ አገርም የመገርሰሷ ዕድል ከፍተኛ እንደሆነ መናገሩ ቢያስደነግጥም ሊደርስ እንደሚችል ማወቁ ለመፍትሔው ፍለጋ ይረዳል።ያንን አይሆንም ብሎና ፈርቶ ማሶገድ ወይም ማስቀረት አይቻልም።በሌላም በኩል አገር ስለምትበታተን ይህንኑ አጥፊ ቡድን አትንኩት እንደለመደው ሲበዘብዝና ሲጨቁን ይኑር ማለትም የሚሻል አይሆንም።የአገርን መበታተን አደጋና የእርስ በርስ ግጭት እሱም የማስፈራሪያ አርጩሜ አድርጎ የሚገለገልበት ነው። የሚፈራውን አደጋ ማስቀረት የሚቻለው በአንድ ዘዴ ብቻ

ነው።ያም በየቦታው የሚካሄደው ሕዝባዊ ትግል በርቀት ላይ የትብብር ድምጽ ከማሰማቱ ባሻገር በዓላማውና በፍላጎቱ የተሳሰረ ሲሆንና በአንድ የጋራ አመራር ሲመራ ብቻ ነው።

አሁን የሚታየው አካሄድ የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው፣ከሱ ጋር የማደርገውን ሂሳብ አወራርጅ ከሚቀጥለው ጋር እተሳሰባለሁ የሚል የብልጦች ስልት  ይመስላል።ከዚያም በላይ በጎሳ እረድፍ የሚካሄድ ትግል ስለሆነ የአንዱ ጎሳ ጥያቄ ለሌላው ጎሳ መልስ የሚሰጥ ሳይሆን እንደውም በጎሳዎቹ መካከል ቅራኔ እንዲያገረሽና የበቀል እርምጃ እንዲስፋፋ ይረዳል፤ያ ደግሞ ሁሉም የሚጎዳበትና አሁን በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን የቀመረውን የአጥፍቶ መጥፋት ዓላማ በተግባር መተርጎም ይሆናል።

“የኦሮሞው ደም ደሜ ነው” “የአማራው ደም ደሜ ነው” “የኮንሶው ደም ደሜ ነው” .... የሚለው መፈክር “የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ደም ደሜ ነው” በሚለው መፈክር ካልተለወጠ ለጥቃቱና ለትግሉ፣ብሎም ለመፈክሩ ሳይቀር ጎሳ የምንለይለት ከሆነ፣ህብረታችንም በጎሳ መፈክር የሚገለጽ ከሆነ አንድ ነን ወይም ለአንድ ዓላማ ቆመናል ለማለት ያስቸግራል፤ እራሳችንንም ማታለል ይሆናል።እርግጥ ነው ወያኔ ለሃያአምስት ዓመት ሲገነባ የቆየውን የልዩነትና የጥላቻ ግምብ ደርምሶት ሊሆን ይችላል፤ግን  ሙሉ ለሙሉ ከልብ የመነጨ ይቅርታና እርቅ የወለደ መሆኑ ያጠራጥራል፤ያማ ባይሆን ኖሮ አማራው እንዲህ አደረገህ በማለት ለጥላቻና ለቂም በቀል እርምጃ በኦሮሞ መሬት ላይ በወያኔ አሻጥር የቆመው የአኖሌ ሃውልት ተገትሮ አይቀርም ነበር።በዳዮቹም ተበዳዮቹም በሌሉበት ዓለምና ጊዜ ምንም የማያውቀው ትውልድ እርስ በራሱ እንዲተላለቅ ቅስቀሳ ማድረግ በጎሰኞች የሚፈጸም ከፍተኛ ወንጀል ነው።ያንን አጥር ሰብሮ መውጣት እውነትም ሕዝብ ለሕዝብ ለመተሳሰቡና ለመተሳሰሩ ማስረጃ በሆነ ነበር። “የ…ደም የኔም ደም ነው” የሚለው መፈክር አንድነትን ለመገንባት የመጀመሪያው ቀና መንፈስ እንጂ የመጨረሻው መሆን አይኖርበትም፤ከዛ ባለፈ ብዙ መሰራት ይኖርበታል። ለአንድነትና ለአብሮነት የምናስብ ከሆነ የጎሳ ማንነታችንን በማጉላት የጋራ የዜግነት መግለጫችን ኢትዮጵያውነታችን  እንዳይደበዝዝ መጠንቀቅና መጠበቅ ይኖርብናል።ያንን ስናረጋግጥ ብቻ ነው፣የእርቅና መቻቻል፣ የሰላምና የእድገት ባለቤቶች ሆነን ልንኖር የምንችለው።

በገሃድ የሚታየው ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ በየአቅጣጫው የጎሳ ወታደራዊ ሃይሎች እየተመሰረቱ መምጣታቸው ነው።ኦሮሞው የራሱን መከላከያ በማደራጀት ላይ ነው፣አማራው በጎበዝ አለቃ ቢመራም ወደ ጦር ሃይል የሚደረስበት ሁኔታ ከፍተኛ ነው።በሌላውም አካባቢ የጎሳ ታጣቂዎች ተሰልፈዋል።ይህ ወዴት ያመራል?ወያኔ መራሹን የጦር ሃይል በጎሳ ሰልፍ በተሰለፈ ሃይል ለመመለስ ይቻላል?ወያኔስ ቢሸነፍ  ይህ በየቦታውና በየጎሳው የተደራጀ ጦር ቀጣዩ ሥራው ምን ሊሆን ነው?በዚያው በተመሰረተበት አኳያ የዚህ ወይም የዚያ ጎሳ የጦር ሃይል ተብሎ ሊቀር ነው?ይህ በልዩነት የተመሰረተ ጦር ወደፊትስ እርስ በርሱ የማይዋጋበት ምን ዋስትና አለ?

አገራችንንም ሕዝቡንም ሊመጣ ከሚችለው ጥፋት ለማዳን የጎሳ ተኮሩ ትግልና የወታደራዊ ምስረታው በኢትዮጵያዊነት መንፈስና በጋራ ዓላማ ላይ የተመሰረተና በአንድ የጋራ አመራር ስር የሚመራ፣ከላይ ለተዘረዘሩት የሕዝብ ጥያቄዎች መልስ ሊሰጥ የሚችል መንግሥትና ስርዓት ለማስፈን በሚያበቃው አቅጣጫ ቢሆን በሁሉም ላይ ሊደርስ ይችላል ተብሎ የሚፈራውን አደጋ ሊያሶግድ ይችላል።በተያዘው መንገድ ግን የሩቅ ትብብር ተማምኖ፣በመፈክር ብቻ በሚገለጥ መረዳዳት ከማዘናጋት ሌላ ወያኔን ጥሎ የተሻለ ለውጥ ለማምጣት የሚቻል አይመስለኝም።የባሰ አደጋ ሊወልድ ይችላል።

ስለሆነም ለአንድ አገርና ሕዝብ፣በአንድነት መታገል፣ትግሉንም የሚመራና የሚያቀናጅ የጋራ ግንባር መፍጠር አይነተኛውና አስተማማኙ መሣሪያ ነው።በየቦታው የሚታየው እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ የሚለው ሽኩቻና አጥፊ ውድድር፣ያልሆኑትን ነኝ እያሉ መወሻከትና ሕዝብን ማማለል ይጎዳል፤ጊዜው ሲደርስ መጋለጡ አይቀርም። ለወያኔና ግብረ አበሮቹ እንጂ ለሕዝቡ ጥቅም የለውም። እውነቱን መናገር ካስፈለገ ሁሉም ተቃዋሚ ደካማ ነው፤ድክመቱን አምኖና ተቀብሎ በጋራ ሃይሉን ቢገነባ መልካም ነው።ያም ብቻ ነው ብዙሃኑን ሊስብና ሊያሳምን ለትክክለኛ ለውጥና ድልም የሚያበቃው አቅጣጫ።አሁን ወያኔ ያለበት ሁኔታ ካለፈው የተዳከመበትና የተፍረከረከበት ወቅት ነው፡፤ይበልጥ ውስጣዊ ቀውሱ እንዲስፋፋና አወዳደቁ እንዲፋጠን፣እንዳያንሰራራ የተቃዋሚው ህብረትና ሃይሉን አስተባብሮ መታገል ወሳኝ ነው።በየቦታው በተናጠል የሚደረገው ስብሰባና ዝግጅት ከሌላው ጋር አብሮ ለመሥራት የሚችሉበትን መንገድ የሚቀይሱበት፣ሊሆን ይገባል።አለበለዚያ ግን በተለመደው መንገድ መሄድ ያው ዞሮ ዞሮ ውጤቱ ዜሮ ይሆናል።

አገሬ አዲስ